# የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎች በካፒታል ገበያ

## መግቢያ

የኮርፖሬት አስተዳደር የካፒታል ገበያ ተዋናዮች የሚመሩበት፣ የሚቆጣጠሩበት እና ተጠያቂነት የሚረጋገጥበት መዋቅራዊ ማዕቀፍ ይመሰርታል። ሀገራችን ወደ ተማከለ የካፒታል ገበያ የተሸጋገረች በመሆኑ በገበያ ተሳታፊዎች ላይ የተጣሉት የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከሩ መጥተዋል። ይህ ጽሑፍ ለካፒታል ገበያ ተዋንያን የሚተገበሩ የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎችን በተለያዩ መመሪያዎች ላይ የተመሠረተ ግምገማ ያቀርባል። በባለሥልጣኑ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያዎች ስር ለአውጪዎች፣ ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ለገበያዎች እና ለሌሎች የገበያ መሠረተ ልማቶች የአስተዳደር እና የቁጥጥር መስፈርቶችን ይመረምራል። ትንታኔው የቦርድ ስብጥርን፣ የዳይሬክተሮችን ተግባራት እና ተጠያቂነቶችን፣ ገለልተኛ የቁጥጥር ዘዴዎችን፣ የኦዲተር የሹመት ፕሮቶኮሎችን እና ለአስተዳደር መዋቅሮች የተወሰኑ ይፋ የማድረግ ግዴታዎችን ይሸፍናል።

## የኮርፖሬት አስተዳደር እንደ ገበያ መሠረተ ልማት

የኮርፖሬት አስተዳደር የተገዢነት ሸክም ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም የካፒታል ገበያ ታማኝነት የሚገነባበት መሠረተ ልማት ነው። ውጤታማ የኮርፖሬት አስተዳደር ሥርዓት የካፒታል ገበያ ተዋናዮች ለባለድርሻ አካላት ጥቅም መቆማቸውን፣ አደጋዎች በአግባቡ መተዳደራቸውን እና የተጠያቂነት ዘዴዎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል። እንደኢትዮጵያ ላሉት ጀማሪ የካፒታል ገበያዎች ከጅምሩ የኮርፖሬት አስተዳደርን አሰራር መዘርጋት ለዘላቂ እድገት አስፈላጊ የሆነውን የኢንቨስተር እምነት ለመገንባት ወሳኝ ነው።

በካፒታል ገበያ አዋጅ የተመዘገቡ ኩባንያዎች የኮርፖሬት አስተዳደር ማስታወቂያዎችና መመሪያዎች እንደሚወጡ ተደንግጎ ይገኛል። በሌላ በኩል ባለሥልጣኑ በተለያዩ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ላይ የአስተዳደር ግዴታዎችን የሚጥሉ በርካታ መመሪያዎችን እና ማኑዋሎችን አውጥቷል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የኮርፖሬት አስተዳደር ማዕቀፍ ከብዙ ምንጮች የመነጨ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በመጀመሪያ የንግድ ሕጉ እንዲሁ ለሁሉም ኩባንያዎች የሚተገበሩ መሰረታዊ የኮርፖሬት አስተዳደር መስፈርቶችን ይደነግጋል። በመቀጠል የካፒታል ገበያ መመሪያዎች ደግሞ ለካፒታል ገበያ ተዋናዮች በዘርፍ የተወሰኑ የአስተዳደር ግዴታዎችን ይጨምራሉ። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ለሚመዘገቡ ኩባንያዎች የኮርፖሬት አስተዳደር ተጨማሪ መስፈርቶችን አካተዋል። ይህ የተደራረበ መስፈርት እና የቁጥጥር ሥርዓት አካሄድ የገበያ ተሳታፊዎች በጥንቃቄ ማሰስ ያለባቸውን አጠቃላይ የአስተዳደር ስርዓት ይፈጥራል።

ይህ ጽሑፍ እነዚህን የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎች በመመሪያ ላይ በተመሠረተ መነጽር ያዳስሳል፣ ይገመግማል። በተለያዩ የካፒታል ገበያ ተዋናዮች ምድቦች ላይ የተጣሉትን የተወሰኑ የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎች ይተነትናል። ጽሁፉ የአውጪዎችን የአስተዳደር ማዕቀፍ በመመርመር ይጀምራል፣ ከዚያም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን እና የገበያ መሠረተ ልማቶችን ግዴታዎች ይዳስሳል።

## ለአውጪዎች የአስተዳደር ማዕቀፍ

በሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ አውጪዎች ለምዝገባ በሚያመለክቱበት ጊዜ ጠንካራ የአስተዳደር መዋቅሮች ያላቸው መሆኑን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። የምዝገባ መግለጫው የአውጪውን የአስተዳደር ዝግጁነት የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ጨምሮ፣ ተገዢነትን፣ ህጋዊነትን እና ግልጽነትን የሚያሳዩ የኮርፖሬት አስተዳደር ተዛማጅ ሰነዶችን ጨምሮ አብሮ መቅረብ አለበት። ተያያዥ ሰነዶች ባለሥልጣኑ የአውጪውን ብቁነት፣ የፋይናንስ አቅም፣ የኮርፖሬት አስተዳደር መዋቅር እና የቁጥጥር ደረጃዎችን አክብሮ ለመስራት ያለውን ዝግጁነት እንዲገመግም ያስችለዋል።

### የአውጪው ቦርድ ስብጥር እና መዋቅር

በንግድ ህጉ መሰረት፣ የአክሲዮን ማህበር ከሶስት እስከ አስራ ሶስት አባላት ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊኖረው ይችላል። የኢትዮጵያ ህግ ባለአክሲዮኖች ያልሆኑ ሰዎች ቁጥራቸው ከጠቅላላ ዳይሬክተሮች አንድ ሶስተኛውን እስካልበለጠ ድረስ የቦርድ ዳይሬክተሮች ሆነው እንዲያገለግሉ ይፈቅዳል። ይህ ድንጋጌ ልዩ እውቀት ያላቸው ገለልተኛ ዳይሬክተሮችን ማካተት ያስችላል፣ ይህም ለጠንካራ የኮርፖሬት አስተዳደር ተግባራዊነት ጉዞ አስፈላጊ ነው።

# የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎች በካፒታል ገበያ

እንደ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች አከናዋኝ፣ የሪል እስቴት ኢንቨስትመንት ፈንዶች አከናዋኝ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ አከናዋኝ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተግባራትን የሚያከናውኑ ኃላፊታቸው የተወሰኑ የግል ኩባንያዎች በካፒታል ገበያ ሥራዎች ውስጥ ሲሳተፉ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲኖራቸው የሚጠበቅባቸው ሲሆን ይህ የኢንቨስተር ጥበቃ ወሳኝ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።

የካፒታል ገበያ የሚሳተፉ ተዋንያን ኃላፊታቸው የተወሰኑ የግል ማህበራት ሲሆኑ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲኖራቸው ለምን ያስፈልጋቸዋል ተብሎ ሲጠየቅ ዋነኛው ምክንያት እነዚህ ድርጅቶች የባለቤቶቹን ገንዘብ ብቻ የሚያንቀሳቅሱ ባለመሆኑ፣ የሕዝብ ጥቅም ያለባቸውን ስራዎች የሚያከናውኑ በመሆናቸው፣ የበርካታ ኢንቨስተሮችን ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱ በመሆናቸው ጥንቃቄ የሚያስፈልግ በመሆኑ ቦርድ መኖሩ ውሳኔዎች ላይ የጋራ ውሳኔ አሰጣጥ እና ተጠያቂነትን ያረጋግጣል

የካፒታል ገበያ ተግባራት የሚያከናውኑ ተቋማት በቦርድ የሚመሩ ከፍተኛ የአስተዳደር መዋቅሮች ያሏቸው ሲሆኑ ቦርድ ውስጥ የተለያዩ ኮሚቴዎች፣ ገለልተኛ ዳይሬክተሮች፣ የኦዲት እና የአደጋ ቁጥጥር ኮሚቴዎች መኖራቸው ወሳኝ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የኩባንያዎች የቦርድ መኖር እና በአንድ ሰው ብቻ አለመመራት የስልጣን ክምችትን ይከላከላል። ይሄ የማጭበርበር፣ የአስተዳደር ብልሹነት ወይም የጥቅም ግጭቶች አደጋዎችን ይቀንሳል።

ባለሥልጣኑ በካፒታል ገበያ የሚሳተፉ ተቋማት ቦርዶች እያንዳንዱ ተቋማት ያላቸውን ወሳኝ መረጃዎች ለሕዝብ ይፋ ሲያደርጉ፣ የደንበኛ ሳቢ መግለጫን ሲያጸድቁ እና መመሪያዎችን አክብረው መስራታቸውን ቦርዶቻቸው እንዲቆጣጠሩ ያዛል። ለእነዚህ ተቋማት ቦርድ መኖሩ የኢንቨስተሮች በራስ መተማመን በመጨመር ገንዘባቸው በግልጽ እና በኃላፊነት የሚተዳደር መሆኑን ያረጋግጥላቸዋል። የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ሆነው ኃላፊታቸው የተወሰኑ የግል ማህበራት ከሕዝብ ወይም ብቁ ከሆኑ ኢንቨስተሮች ገንዘብ ስለሚያሰባስቡ፣ በአስተዳደር ግዴታዎች ረገድ እንደ አክሲዮን ኩባንያዎች የሚቆጠሩ ናቸው። ስለዚህ ጠንካራ አስተዳደር፣ ቁጥጥር እና የኢንቨስተሮች ጥበቃን ለማረጋገጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ መኖሩ ወሳኝ መሳሪያ ነው።

## የዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባራት እና ተጠያቂነቶች

የአክሲዮን ማህበራት ዳይሬክተሮች በንግድ ሕጉ መሠረት በርካታ ዋና ዋና ተግባራትን ያከናውናሉ። እነዚህም ዳይሬክተሮች ኃላፊነታቸውን በብቃት እና በጥንቃቄ እንዲወጡ የሚያስገድድ የትጋት ግዴታ፤ ገለልተኛ ውሳኔ የመስጠት ግዴታ፤ ዳይሬክተሮች የኩባንያውን ስኬት በሚያበረታታ እና ሁሉንም ባለአክሲዮኖች በሚጠቅም መንገድ እንዲሠሩ የሚያዝ የታማኝነት ግዴታ እና የጥቅም ግጭቶችን የማስወገድ ግዴታን ያካትታል። ዳይሬክተሮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተቀናቃኝ ንግድ ውስጥ ከመተባበር ወይም ከመሳተፍ ወይም ከኩባንያው ጋር ከመወዳደር የተገደቡ ወይም የተከለከሉ ናቸው። እንዲሁም የኩባንያውን ንብረት፣ መረጃ ወይም እድሎችን መጠቀምን ጨምሮ ወደ ጥቅም ግጭቶች ሊያመሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ማስወገድ አለባቸው። ዳይሬክተሮች የጥቅም ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ፣ የጥቅማቸውን ተፈጥሮ እና መጠን ለሌሎች ዳይሬክተሮች የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

የአክሲዮን ማህበር በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ ከተመለከተ የተቆጣጣሪ ቦርድ ማቋቋም ይችላሉ። የተቆጣጣሪ ቦርዱ ከሶስት እስከ አምስት አባላት ያሉት ሲሆን የኩባንያው ባለአክሲዮኖች መሆን አለባቸው። አባላት የሚሾሙት እና ተጠያቂ የሚሆኑት በባለአክሲዮኖች አጠቃላይ ስብሰባ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ማገልገል አይችሉም። የተቆጣጣሪ ቦርዱ ስልጣን ሰነዶችን እና መረጃዎችን ማስቀረብ፣ የኩባንያውን ጉዳዮች መመርመር፣ በኩባንያው ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ድርጊቶችን መመርመር፣ የአስተዳደር አፈጻጸምን መቆጣጠር እና ለጠቅላላ ስብሰባ ሪፖርቶችን ማቅረብን ያካትታል። ይህ ባለሁለት ደረጃ የቦርድ መዋቅር አማራጭ ቢሆንም ተጨማሪ የአስተዳደር ቁጥጥር ደረጃ ይሰጣል።

## የባለአክሲዮኖች መረጃዎችን ይፋ የማድረግ ግዴታዎች

ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻቸው ለሕዝብ ግብይት ያቀረቡ ኩባንያዎች ባለአክሲዮኖች ጉልህ የሆነ የይፋ ማድረግ ግዴታዎችን ያስተዋውቃል። "ጥቅም ያለው ሰው" ማለት በቀጥታ፣ በተዘዋዋሪ ወይም ከሌሎች ጋር በመተባበር የተመዘገበ ኩባንያ ካፒታል ላይ አምስት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የያዘ ማንኛውም ሰው ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ሰነዱን ከገዙበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት በአምስት ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ፣ ለገበያው እና ለአውጪው የተረጋገጠ መግለጫ ማቅረብ አለባቸው። መመሪያው የዋናዋና ባለአክሲዮኖችን የድምጽ መስጫ መብቶች፣ ለቁጥጥር የሚያበቃ አክሲዮን ባላቸው ባለአክሲዮኖች እና በአውጪው መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እና የቁጥጥር ለውጥ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ይፋ ማድረግን ግዴታ ይጥላል። ባለአክሲዮኖች እነዚህን መረጃዎች ይፋ ባለማድረግ በባለሥልጣኑ፣ በገበያው ወይም በሶስተኛ ወገኖች ለሚደርስጉዳት ተጠያቂነትን ያስከትላል።

# የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎች በካፒታል ገበያ

## ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎች

የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የፈቃድ አሰጣጥ እና የቁጥጥር መመሪያ ፈቃድ ላላቸው የካፒታል ገበያ ተሳታፊዎች አጠቃላይ የአስተዳደር ማዕቀፍ ያቋቁማል። መመሪያው አስራ አምስት የተለያዩ የፈቃድ ዓይነቶችን የሚለይ ሲሆን እያንዳንዳቸው ለተወሰኑ የአስተዳደር መስፈርቶች ማሟላት የሚጠበቅባቸው ናቸው።

መመሪያው ፈቃድ ያላቸው አገልግሎት ሰጪዎች ኃላፊነቶች እና ግዴታዎች ዝርዝር ደንቦችን ያቀፈ ሲሆን ይህም የአስተዳደር እና የሥነምግባር መርሆዎችን ያካትታል። ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ የሚጠይቅ አመልካች የአክሲዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን ለአስተዳደሩ ኃላፊነት ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊኖረው ይገባል። መመሪያው ለአገልግሎት ሰጪዎች የብቃት ማዕቀፎችን እና የስነ-ምግባር ደንቦችን ይሸፍናል።

ባለሥልጣኑ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ ለሚጠይቁ ዝግጁነታቸውን ለመፈተሽ የራስ ግምገማ መሳሪያ አዘጋጅቷል። ግምገማው ለእያንዳንዱ የሚመለከተው የፈቃድ አይነት ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ የአስተዳደር እና ሌሎች መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ ነው። ይህ የራስ ግምገማ ሥርዓት በቅጹ መልክ የተዘጋጀ ሲሆን በመመሪያው ክፍል 4 ተመልክቶ ይገኛል። ይህ ቅጽ የአስተዳደር መዋቅርን ጨምሮ የአስተዳደር መስፈርቶችን በተለይም ይመለከታል። የራስ ግምገማ አሰራር ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ድርጅት ጠንካራ የኮርፖሬት አስተዳደር መዋቅሮች ያለው መሆኑን ማሳየት አለበት።

## ቀጣይነት ያላቸው የአስተዳደር ግዴታዎች

ፈቃድ ያላቸው የአገልግሎት ሰጪዎች በወጣው የቁጥጥር መመሪያ መሠረት ቀጣይነት ያላቸው የአስተዳደር ግዴታዎች ተገዢ ይሆናሉ። መመሪያው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ እና የተዛማጅ ውሎች ገበያዎችን፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ፣ ክፍያ አጣሪ እና ፈጻሚ ኩባንያ ጨምሮ ፈቃድ እና እውቅና ላላቸው የገበያ ተሳታፊዎች ተፈጻሚ የሚሆን ነው። መመሪያው ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት የፋይናንስ ጤናማነት፣ የቦርድ ውጤታማነትን እና የአደጋ አስተዳደር ስርዓቶችን ለማረጋገጥ ተገቢ የአስተዳደር መዋቅሮችን እንዲያቋቁሙ ያዛል። ቁልፍ የተገዥነት (ህግ ማስከበር) ዘርፎች የአንድን አገልግሎት ሰጪ የአስተዳደር ስርዓቱን ከፋናንስ መረጋጋት እና ከንግድ አሰራር ብቃት ጋር አጣምረው የያዙ ናቸው።

## የገበያው እና የገበያ መሠረተ ልማቶች የአስተዳደር መስፈርቶች

የባለሥልጣኑ ቁጥጥር መመሪያ በተለይ ለግብይት ሥርዓቶች ጥብቅ የአስተዳደር መስፈርቶችን ያስቀምጣል። ይህም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎችን፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያዎችን እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎችን ያካትታል። እነዚህ አካላት የገበያውን የቁጥጥር እና የክትትል ግዴታዎች የሚቆጣጠር ገለልተኛ ኮሚቴ ማቋቋም እንዳለባቸው ባለሥልጣኑ ባወጣው የቁጥጥር እና ክትትል ጋይድላይን ተመልክቶ ይገኛል።

ይህ ኮሚቴ የገበያው የግብይት ሥርዓቶች የቁጥጥር እና የክትትል ግዴታዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ መወጣትን ለማረጋገጥ የአስተዳደር ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነት ያለው ኮሚቴ ነው። ኮሚቴው በጋይድላይኑ መሰረት ተጨባጭነትን ለማረጋገጥ እና የገበያ ታማኝነትን ለመጠበቅ፣ ውጤታማ አስተዳደር እና ቁጥጥርን ለማረጋገጥ ገለልተኝነቱ እና ሥልጣኑ የተጠበቀ ራሱን የቻለ ኮሚቴ ወይም የቦርድ ደረጃ ኮሚቴ ሆኖ ይቋቋማል። የዚህ ኮሚቴ ገለልተኝነት የጥቅም ግጭቶችን ለማስወገድ እና ነጻ የውሳኔ አሰጣጥን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ኮሚቴው ራሱን የቻለ አካል ሆኖ የሚሰራ ሲሆን ኃላፊነቶቹን በብቃት ለመወጣት በቦርድ ደረጃ ስልጣን ተሰጥቶታል።

ሰነዱ ኮሚቴው ገለልተኛ መሆን አለበት ሲል ከገበያው የሥራ ክንውኖች እና የግብይት ተግባራት የተለየ መሆን አለበት ለማለት ነው። ሰነዱ የተወሰኑ ግለሰቦች በዚህ ኮሚቴ ውስጥ በአባልነት እንዳያገለግሉ በግልጽ ይከለክላል። እነዚህ ግለሰቦች ከአስተዳደር ወይም ከዕለታዊ ሥራዎች ጋር የተቆራኙ ማናቸውንም ሰው፣ የአሁኑን ወይም የቅርብ ጊዜ ሠራተኞችን እና ሥራ አስፈፃሚዎችን፣ እና ገለልተኛነትን ሊያበላሹ የሚችሉ ግንኙነቶች ያላቸውን ግለሰቦችን ያካትታል። ከዚህ በተጨማሪ በሰነዱ ለፖለቲካ የተጋለጡ ሰዎች ተብለው የተገለጹት ከፍተኛ ፖለቲከኞች፣ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣ የፍትህ ወይም ወታደራዊ ከፍተኛ አመራር፣ ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሥራ አስፈፃሚዎች በእነዚህ ገለልተኛ የቁጥጥር እና ክትትል ኮሚቴዎች ውስጥ እንዳያገለግሉ የተከለከሉ ናቸው።